# ሰባተኛ ትምህርት ከየካቲት 4 — 10 Feb 11—17

## መንፈስ ቅዱስና የመንፈስ ፍሬ

**ሰንበት ከሰዓት**

ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ዮሐ. 15:1-11፣ ገላ.5:22፣ 1ቆሮ. 13፣ ሮሜ 14:17፣ ኤፌ. 5:9፣ ማቴ. 5:5፡

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡-**

**"የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው፡፡ እንደነዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም" (ገላ. 5:22-23)፡፡**

የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የክርስትና ሕይወት እውነተኛ ባህሪ ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ከጠቀሳቸው ከእነዚህ ዘጠኝ የተለያዩ ገጽታዎች ካሏቸው ፍሬዎች ውስጥ ቢያንስ አንዱ ሙሉ ለሙሉ በአማኙ መታየት ይኖርበታል፡፡ አንድ ሰው የሚሰጡትን መንፈሳዊ ስጦታዎችና መክሊቶች ተጠቅሞ ለእግዚአብሔር ስለሚሠራው ሥራ የመንፈስ ፍሬ የሚነግረን ነገር ባይኖረውም ነገር ግን ግለሰቡ እንዴት ለእግዚአብሔር ሊኖር እንደሚገባ በግልጽ ያሳየናል፡፡ ስለ ግለሰቡ ማንነት ፍንጭ ይሰጠናል፡፡ በገላ. 5:22-23 የተጠቀሱት ሁሉም መልካም ምግባሮች በየሱስ ውስጥ ተገልጠው መታየት ችለዋል፡፡ በመሆኑም የመንፈስ ፍሬ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እውን መሆን የቻለው በእኛ ውስጥ የሚኖረው የየሱስ ክርስቶስሕይወት ነው፡፡

የመንፈስ ፍሬ ሙሉ ለሙሉ ሰብዓዊ በሆነ ጥረት ብቻ ልናገኘው የምንችለው ነገር አይደለም፡፡ አንዳንዶቹን ተመሳሳይነት ያላቸውን መልካም ምግባሮች በጎ ፈቃደኝነትን አብልጠን በመለማመድ ልናፈራቸውም ሆነ ገልጠን ልናሳያቸው ብንችልም ነገር ግን ይህ ሁኔታ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ከሚሠራው ጋር ተመሳሳይ አይደለም፡፡ እኛ በራሳችን የምናፈራው ከእውነተኛው ፍሬ ጋር ሲተያይ ከሰው ሠራሹ አብለጭላጭ አትክልትና ፍራፍሬ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ከሩቅ ሲታይ የሚያምርና የሚያስጎመዥ የሚመስለው ፍሬ ወደ አፍንጫ ሲያስጠጉት ከእውነተኛው ጋር ፍጹም አይገናኝም፡፡ እውነተኛ አትክልትም ሆነ ፍራፍሬ ሰው ሠራሽ አይደለም--ከግንኙነትን ባሻገር የሚያድግና የሚፈካ እንጂ፡፡ መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ከየሱስ ጋር ግንኙነት እንድንፈጥር ሲያደርገን የእርሱ ጸባይ በእኛ ውስጥ መገለጥ ይጀምራል፡፡

*እሑድ የካቲት 5* *Feb 12*

## ፍሬ ማፍራት የሚቻልባቸው ሁናቴዎች

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡-- ዮሐ. 15፡1-11፡፡ ፍሬ ማፍራት የሚቻለው ከየሱስ ጋር ሕያው ግንኙነት በመመስረት ብቻ የሆነው ለምንድን ነው? ለየሱስ ታማኝ መሆን አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ከእርሱ ጋር አብረን መሆን የምንችለው እንዴት ነው?

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

በክርስትና ሕይወት እውነተኛ ፍሬ የምናፈራበት ቀዳሚ ምስጢር በክርስቶስ መኖር ነው፡፡ ከክርስቶስ ውጪ እውነተኛ የመንፈስ ፍሬ ማፍራት አንችልም፡፡ የመንፈስ ፍሬ ከውጪ የሚጫንብን ነገር ሳይሆን ነገር ግን በውስጣችን የሚኖረው የክርስቶስ ሕይወት ውጤት ነው፡፡ የመንፈስ ፍሬ--የወይኑ ግንድ ከሆነው ክርስቶስ፤ ቅርንጫፍ ወደ ሆኑት አማኞች የሚፈስ የእርሱ ሕይወት ውጤት መሆኑን የሱስ በዮሐ. 15፡1-11 ይነግረናል፡፡ ፍሬውን የሚያሳድገው በየሱስ የሚሠራው አምላካዊ ሥራ ነው፡፡

የአማኙ ኃላፊነት በክርስቶስ መኖር ነው፡፡ ክርስቶስ በሃሳባችን ውስጥ ሲያድር በድርጊቶቻችን የሚገለጥ ይሆናል፡፡ የሱስ በእኛ ውስጥ ሕያው ሆኖ ይኖራል፡፡ ክርስቶስ በእኛ ውስጥ የኖረው ህይወት በውስጣችን ፍሬ ስለሚያፈራ በምላሹ የእርሱን ጸባይ የምናንጸባርቅ እንሆናለን፡፡

የመንፈስ ፍሬ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በክርስቶስ ተከታዮች ውስጥ የሚያፈራ የየሱስ ጸባይ ነው፡፡ ክርስቶስ በእኛ ውስጥ ሲያድር--በመንፈስ እንኖራለን እንጂ የሥጋን ምኞት አንፈጽምም (ገላ. 5፡16)፡፡

የሱስ እንዲህ ሲል ተናግሮአል "እንዲሁም ጥሩ ዛፍ ሁሉ ጥሩ ፍሬ፣ መጥፎ ዛፍ ግን መጥፎ ፍሬ ያፈራል፡፡ ጥሩ ዛፍ መጥፎ ፍሬ፣ መጥፎም ዛፍ ጥሩ ፍሬ ማፍራት አይችልም" (ማቴ. 7፡17-18)፡፡ ጥሩው ፍሬ ከየሱስ ጋር በሚኖረን ግንኙነት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የምናፈራው የተለመደው ፍሬ ነው፡፡ ከመንፈስ ጋር ከልብ የሆነ ሥር የሰደደ ግንኙነት ስንፈጥር የመንፈስ ፍሬ በሕይወታችን ውስጥ በግልጽ የሚታይ ይሆናል፡፡ ጸባያችን--በምንናገረው፣ በምናደርገውም ሆነ እንዲሁም በምናስበው ሳይቀር የየሱስ ክርስቶስን ጸባይ ለማንጸባረቅ የተለወጠ ይሆናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጆች መለያ ጸባይ የሆኑትን ምግባሮች እያጎለበትን በድል የምንኖርበትን ኃይል ይሰጠናል፡፡

ጳውሎስ በ 2ጢሞቴ. 3፡5 "ኃይማኖታዊ መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፡፡" በማለት የሚገልጻቸው ሰዎች አሉ፡፡ በኃይማኖታዊ ሕይወትና በመንፈስ ቅዱስ በተሞላ ሕይወት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ራሳችን የትኛውን ዓይነት ሕይወት እየኖርን እንደ ሆነ እንዴት ማወቅ እንችላለን?

*ሰኞ የካቲት 6* *Feb 13*

## ፍቅር – የመንፈስ ፍሬ

እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡-- ገላ. 5፡22፣ 1ቆሮ. 13፡፡ **ፍቅር የመጀመሪያና ቀዳሚ የመንፈስ ፍሬ ገጽታ የያዘው ለምንድን ነው? ፍቅር--ከእርሱ በመቀጠል በተቀመጡት በሁሉም የመንፈስ ፍሬዎች ላይ እንዴት ተጽእኖ ይኖረዋል?**

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የተለያየ ጸባይ ካላቸው የመንፈስ ፍሬዎች ጋር ገጣሚ የሆነውና ሁሉንም በበላይነት የሚቆጣጠረው ፍቅር በእያንዳንዱ ፍሬ ውስጥ ገብቶ የመሰራጨትና የመስፋፋት ልዩ ባህሪ አለው። እንደውም ሌሎቹ የተጠቀሱት ፍሬዎች ሁሉ እንደ ፍቅር መገለጫ ሆነው መታየት ይችላሉ። እግዚአብሔር ፍቅር እንደ መሆኑ (1ዮሐ. 4፡8) ከሁሉም የላቀው የክርስቲያን ምግባር ፍቅር ነው (1ቆሮ. 13፡13)። የእግዚአብሔር ፍቅር የእያንዳንዱ በጎነት መሰረትና ምንጭ ነው። አምላካዊው ፍቅር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ወደ ልባችን ይፈሳል (ሮሜ 5፡5)። ፍቅር የእግዚአብሔር ልጆች የመሆናችን ማስረጃ ነው።

ይህ ዓይነቱ ፍቅር ከሰብዓዊው ፍቅር በእጅጉ የተለየ ነው። ሰዎች በራሳቸው ጥረት ሊያፈሩት አይችሉም። ይህ ፍቅር በክርስቶስ የመኖር ውጤት እንደመሆኑ ደግና የማይገባን ነው። ይህ ፍቅር ብቻ ልብን የመለወጥ ኃይል አለው። ኃጢአተኛውን ወደ ንስሐ የሚመራና ውስጡን ለተሻለ በጎ የሚያነሳሳ ርኅሩኅ--ደግሞም ጠንካራ ባህሪ ያለው መለኮታዊ ፍቅር ነው። ፍቅር ቀድሞ ጠላት የነበሩትን እንኳ ዳግመኛ የማስተሳሰር ኃይል አለው (ሉቃስ 6፡27-28)። ስለዚህ አንዳችን ለሌላው ፍቅር ሲኖረን ክርስቲያኖች በእርግጥ የየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች መሆናችንን ዓለም ያውቃል (ዮሐ. 13፡35)። ይህ የፍቅር ፍሬ ክርስቲያኖች ሌሎችን እንዲያስተውሉና ስሜታቸውን እንዲጠብቁ ይመራቸዋል።

በ1ቆሮ. ምዕ. 13 የምናገኘው ቁልፍ የፍቅር መግለጫ በምዕራፍ 12 እና 14 መካከል መቅረቡ አስደሳችና አስገራሚ ትርጉም እንዲይዝ ያደርገዋል። ሁለቱ ምዕራፎች ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሲናገሩ ምዕራፍ 13 ግን በፍቅር ላይ--ይኸውም የመንፈስ ፍሬ በሆነው ፍቅር ላይ አጽንኦት ይሰጣል። ታላላቆቹ ስጦታዎችም ቢሆኑ ያለ ፍቅር ምንም ናቸው። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የፍቅር ፍሬ ካላፈሩ አቅመ ቢስና እግዚአብሔር ያቀደውን በረከት ማምጣት የሚሳናቸው ይሆናሉ። ስለዚህ ፍቅር ሁሉንም የመንፈስ ፍሬዎች በአንድ አጣብቆ በመያዝ የተባበረ ምሉዕ ገጽታ የሚያላብስና ለምናደርገው ሁሉ ተጨባጭነትን የሚሰጥ ነው።

**የፍቅር ጉድለት ወይም እጦት የሚስተዋልበት የሕይወትዎ ክፍል የትኛው ነው? በየቀኑ ከሚገናኟቸው ሰዎች ጋር በፍቅር ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እንዲኖርዎ መንፈስ ቅዱስ በፍቅር ይሞላዎት ዘንድ ይጠይቁት። እግዚአብሔር በሌሎች ሰዎች አማካይነት ፍቅሩን እንደሚገልጽልን አይዘንጉ። ለሌሎች ያሎትን ፍቅር እንዴት ማሳየት ይችላሉ? በመንፈስ ፍሬ በተገለጡት በሌሎቹ በጎ ምግባሮች ውስጥ ፍቅር ተጽእኖ የሚኖረው እንዴት ነው?**

*ማክሰኞ* *የካቲት 7* *Feb 14*

## ደስታ፣ ሰላምና ትዕግሥት

በሮሜ 14፡17 ይህን ጥቅስ እናገኛለን፡--“የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም፣ በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ሐሤት ነው እንጂ የመብልና የመጠጥ ጉዳይ አይደለም።” ይህ ማለት ሐሤት--እግዚአብሔር ለሰጠን በረከት፣ ታላቅ ምኅረትና ይቅርታ የምናሳየው የፍቅር ምላሽ ነው።

ብዙውን ጊዜ የሰብዓዊው ደስታ ትኩረት በምድራዊው ነገሮች ላይ በመሆኑ ዙሪያችንን በከበቡን ሁናቴዎች ተጽእኖ ስር የወደቀ ነው። ነገር ግን የመንፈስ ፍሬ ውጤት የሆነው ደስታ የታነጸው በጥልቅ መሰረት ላይ በመሆኑ ትኩረቱ በእግዚአብሔርና እርሱ ባደረገልን ነገሮች ላይ ነው። በዚህ የተነሳ በዙሪያችን የከበቡን ሁናቴዎች ለመነሳሳቱ መንስኤ መሆን አይሆኑም። እኛ እንደ እግዚአብሔር ሕዝብነታችን በሐሴት የተሞላን ልንሆን የተገባ ነው። ምንም እንኳ ወዳጃዊ ፈገግታ ብዙ ትርጉም ሊኖረው ቢችልም፤ ቀኑን ሙሉ በዚህ ሁኔታ እንዋል ማለት ግን አይደለም። ሆኖም እግዚአብሔርን ማመናችን እርሱ ላደረገልንና

በእኛ ውስጥ እየሠራ ላለው ሥራ ቃላት ሊገልጹት በማይችሉት ደስታ--ሐሴት እንድናደርግ አብልጦ ምክንያት ሊሆነን ይችላል። ንቁና ብርቱ እምነት የመንፈሳዊ ደስታ መንስኤ ነው።

**እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡-- ዮሐ. 14:27፣ ሮሜ 14:17። ሰላም ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጋር ተዛምዶ ሊኖረው የሚችለው እንዴት ነው?**

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ሰላም ከደስታ ይልቅ አብልጦ በውስጣችን መቆየት ይችላል። ሰላም በጌታችን በየሱስ ክርስቶስ ላይ ባለን እምነት ያገኘነው ጽድቅ ውጤት ነው (ሮሜ 5:1)። ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ሲኖረን መንፈስ ቅዱስ ለሌሎች ሰላማዊና ትዕግሥተኛ እንድንሆን ይመራናል። የሰላም አምላክ (ፊልጵ. 4:9) በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ከእኛ ጋር ስለሚሆን ጸበኞችና በቀለኞች አንሆንም። ይልቁንም ከማንኛውም ሰው ጋር በሰላም ለመኖር ያላሰለሰ ጥረት እናደርጋለን (ሮሜ 12:18)።

**በ2ጴጥ. 3:9 ላይ እንደ ተገለጸው ትዕግሥት የእግዚአብሔርን ጸባይ የሚያንጸባርቀው እንዴት ነው?**

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ትዕግሥት በሰብዓዊው ፍጡር ውስጥ እንደ ልብ የሚገኝ ጸባይ አይደለም። ነገሮች መልካም ገጽታ ባልያዙበት ሁናቴ ውስጥ እንኳ ሌሎችን ታግሶ ማለፍ ነው። በእርግጥ በፈተና ውስጥ ሆነንም--ብቻችንን አልተተውንም። እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ደግፎ ይይዘናል--በመጨረሻው ዘመን የሚኖሩ አማኞች መለያ ምልክት የሆነውን ትዕግሥት አብልጦ በውስጣችን ያኖራል።

**ደስታ፣ ሰላምና ትዕግሥት። ከዚህ ፍሬዎች ምን ያህሉን በሕይወትዎ ተለማምደዋል? ከእነዚህ ፍሬዎች አብልጠው መሥራት የሚኖርቦት በየትኞቹ ዙሪያ ነው?**

*ረቡዕ የካቲት 8* *Feb 15*

## ቸርነት፣ በጎነትና ታማኝነት

**ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡--ከልብ የመነጨ ቸርነት በሌሎች ላይ ብርቱ ተጽእኖ ያለው ለምንድን ነው? እግዚአብሔር ከሰብዓዊው ፍጡር ጋር ባለው ግንኙነት በጎነቱን የሚመለከቱት የቱ ላይ ነው?**

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ሊደረግ የሚገባውን የሚገልጽ ቃል ነው። ከእርሱ ርቀን በመጓዝ በምንሠራው አሳዛኝ ተግባር እግዚአብሔር ጥብቅ ሊሆን ቢችልም ነገር ግን ገና ትምህርት እየቀሰመ እንዳለ ጨቅላ ልጁ በፍቅር ዐይኖቹ ይመለከተናል (ሆሴ 11:1-4)። ምናልባት በክርስትና ምስክርነታችንና አገልግሎታችን በተደጋጋሚ የሚስተዋል ብርቱ ተግዳሮት ክፍት ሊሆን ይችላል። ደግ መሆናችን አንዳችም ወጪ የማያስወጣን ቢሆንም ነገር ግን የሌላውን ሰው የልብ በር መክፈት ይችላል። የቱንም ያህል ጠንካራ ተቺዎች ወይም በብርቱ የምንገስጽ ልንሆን ብንችል--ሰዎች የከፋ ጉድለት ያሳዩበት ሁናቴ ሲከሰት ክፉ ልንሆንባቸው ግን ፈጽሞ አይገባም። ሰዎችን ደግነት በተሞላው አኳኋን መገሰጽ መቻል ምናልባትም የታላቅ ባህሪ ባለቤትነት ምልክት ነው።

**በኤፌ. 5:9 በጎነት ታጅቦ የቀረበው በየትኞቹ ቃላት ነው?**

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

በጎነት በተግባር የተገለጸ ፍቅር ነው። በመንፈስ ፍሬነት እየበለጸገ የሚሄደው በጎነት ሥራንና ድርጊትን ያካትታል። ለሌሎች የሚደረግ በተግባር የተገለጸ ፍቅር በጎነት ነው። መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ሲያድር በጎነት በማያቋርጥ አዎንታዊ ፍሰት ወደምንገናኛቸው ሰዎች ይደርሳል።

ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡--ገላ. 5፡22። ከእግዚአብሔር ጋር ባለን መንፈሳዊ ጉዞ ታማኝነት በእጅጉ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ከላይ በቀረበው ጥቅስ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆነውን ታማኝነት እናገኛለን። ታማኝነት--እምነት የሚጣልበት ወይም ሊታመን የሚችል የሚል ፍቺ አለው። ታማኝ የሆኑ ሰዎች ቃል የገቡትን ነገር ይፈጽማሉ። በተጨማሪ ታማኝነት “ታማኝ ምስክር” (ራእ. 1፡5) ተብሎ የተጠራው የየሱስ ክርስቶስና የሰጠውን ተስፋ የሚጠብቀው፣ በሥራው ሁሉ ታማኝ የሆነው የእግዚአብሔር አብ ጸባይ ነው (1ቆሮ. 1፡9፣ 10፡13፣ 1ተሰ. 5፡24፣ 2ተሰ. 3፡3)። ታማኝ ስንሆን አምላካዊውን አምሳል በሕይወታችን እናንጸባርቃለን። “ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበ ሥራ መሥራታችን ሳይሆን ለሥራው የሚኖረን ተነሳሽነት በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ አለው። እግዚአብሔር ለበጎነትና ለታማኝነት የሚሰጠው ሽልማት ክንውን ካገኘው ሥራ በላይ ነው።”–Ellen G. White, Testimonies for the Church, vol. 2, pp. 510, 511.

*ሐሙስ የካቲት 9* *Feb 16*

## ገርነትና ራስን መግዛት

**እነዚህን ሁለት ጥቅሶች ያንብቡ፡--ገላ. 5፡23፣ ማቴ. 5፡5። የዋህነት፣ ትህትና ወይም ገርነት ክርስቶስን ለሚመስል አመራር በእጅጉ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?**

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የዋህነት፣ ትህትና ወይም ገርነት--ደካማነትን አይገልጽም ወይም ደካማ የሚል ፍቺ የለውም። ፈሪ ወይም የአመራር ጥበብ የጎደለው ማለትም አይደለም። ይልቁንም ኃይለኛ የእግዚአብሔር ሕዝቦች መሪ የነበረው ሙሴ በምድር ካሉ ሰዎች ሁሉ ትሑት እንደ ነበር ተጠቅሶአል (ዘኁ. 12፡3)። ገር ሰዎች--ሁከተኞች፣ ጸበኞች ወይም ራስ ወዳድ ጠብ-ጫሪዎች አይደሉም። በዚህ ፋንታ የዋህ በሆነ መንፈስ ያገለግላሉ። ገርነት በውስጥ ያለው እምነትና መተማመን ውጫዊ መገለጫ ሊሆን ይችላል--በራስ ሳይሆን ነገር ግን በአማኙ ውስጥ በሚሠራው በእግዚአብሔር ኃይል። ነገር ግን ሁከተኞችና ተጨቃጫቂዎች በውስጣቸው የጎደለውን የደኅንነት ማጣት ስሜትና ፍርሐት ለመሸፈን--ከገርነት በተቃራኒ ያሉትን እነዚህን ባህሪያት በደማቁ ያሳያሉ።

**እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡--ገላ. 5:23፣ ምሳ. 16:32። ራሳችንን እንዴት መግዛት እንዳለብን መለማመድ ሳንችል ስንቀር ምን ዓይነት የከፋ ሁናቴ ሊገጥመን ይችላል? ራሳችንን የምንገዛና መሻታችንን መቆጣጠር የምንችል ስንሆን ምን ዓይነት በረከቶችን በሕይወታችን ማግኘት እንችላለን?**

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

በመጨረሻ የተጠቀሰው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ራስን መግዛት ነው። መቼም ማንም ቢሆን ራሱን የተሻለ ሁናቴ ላይ ለማኖር ከአንዱ ወይም ከሌላው ነገር ጋር ፍልሚያ ውስጥ መግባቱ አይቀሬ ነው። አንድ ሰው አንድን ከተማ ወይም ማኅበረሰብ፣ ወይም ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ከመምራቱ አስቀድሞ የራሱን መንፈስ መቆጣጠሩ የግድ ይሆናል። እውነተኛ መሻትን መግዛት በምግብና በመጠጥ ላይ ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዱ የሕይወት ምዕራፍ ጭምር ነው።

ከላይ የተጠቀሱት በሙሉ የአንድ መንፈስ ፍሬ አካል ናቸው። እግዚአብሔር በሕይወታችን ስለሚሠራው ሥራ የሚነግረን መጽሐፍ ቅዱስ--ግብረገባዊ ገጽታ ያለው ቅድስና ከካሪዝማቲክ ስጦታዎች በላይ እንደሆነ ይገልጽልናል። በአማኙ ሕይወት መስተዋል ያለበት ዋናው ቁም ነገር ሙሉ ለሙሉ ክርስቶስን የሚመስል ሕይወት መኖሩ ነው። የመንፈስ ፍሬ በግልጽ የሚስተዋል አንድነት በቤተ ክርስቲያን ማምጣቱ በየትኛውም ስፍራ በሚገኙ አማኞች መካከል መታየት የሚችል መለያ ምልክት ነው።

አብልጠው ራስዎን መግዛት ስለሚኖርብዎ የሕይወትዎ ክፍሎች አሰብ ያድርጉ። ምናልባት በአንደኛው ጠንካራ ሆነው ነገር ግን በሌላኛው ድካም ይኖሮት ይሆን? እግዚአብሔር በሚሰጥዎት ኃይል በሁሉም ክፍሎች ላይ ብርታት መኖሩ በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? መልስዎን በሰንበት ትምህርት ጥናት ላይ ይዘው ለመምጣት ይሞክሩ።

*አርብ* *የካቲት 10* *Feb 17*

## ተጨማሪ ሃሳብ:-

“በገላ. 5:22-23 የምናገኛቸው ጥቅሶች ዛሬ በምንግባባበት በዘመነው ቋንቋ የሚከተለው አንደምታ ሊኖራቸው ይችላል፡ ‘የመንፈስ ፍሬ አፍቃሪና ተወዳጅ የሆነውን ጸባይ የያዘ--አስደሳች፣ ፍልቅልቅና ደስተኛ ስሜትን የሚያንጸባርቅ--ጸጥተኛና ሰላማዊ አእምሮን እንዲሁም የተረጋጋ አኳኋንን የሚያሳይ--በተንኳሽ ሁናቴዎችና ፈታኝ በሆኑ ሰዎች መሃል ይቅር ባይነትንና ትዕግሥተኝነትን ያነገሠ--ለአርቆ አሳቢና አዛኝ፣ ለብልህና ጥንቁቅ ረዳትነት ዋጋ የሰጠ--በቸርነት የተሞላውን ፍርድና በጎነት የተንጸባረቀበትን ለጋስነትን የገለጠ--ምንም ይምጣ ምን ታማኝና እምነት የሚጣልበት ሆኖ መገኘትን ያሞካሸ--ስለ ሌሎች ደስታ ራሱን ችላ የሚለውን ትሁት ያሳየ--የፍጽምና የመጨረሻው ምልክት የሆነውን በሁሉም የሕይወት ፈርጆች ራስንም ሆነ መሻትን መግዛት መቻል ያደፋፈረ ነው። እነዚህ የመንፈስ ፍሬ ጸባዮች ናቸው። እያንዳንዱ ነገር ፍሬ የተሰኘው ቃል አካል ነው። ታዲያ የእነዚህ ፍሬዎች ባለቤት መሆን የሚቻለው ብርቱ ጥረት በማድረግ ሳይሆን በእርሱ በመኖር--በመጨነቅ ሳይሆን በእርሱ በመታመን--በሥራ ሳይሆን በእምነት ብቻ ነው።’ ”–S. Chadwick, in Arthur Walkington Pink, The Holy Spirit (Bellingham, Wash.: Logos Bible Software, n.d.) , chapter 30.

“የእውነት ፍቅር በልብዎ ካለ ከአንደበትዎ የሚወጣውም እውነት ይሆናል። በየሱስ ያገኙትን የተባረከ ተስፋ ይናገራሉ። ፍቅር በልብዎ ካለ ወንድምዎ እጅግ ከፍ ባለው የተቀደሰ እምነት ጸንቶ እንዲቆም

አጥብቀው ይመኛሉ። በወንድሞ ወይም በጓደኛዎ ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ጎጂ ቃል ከተናጋሪው ከተሰነዘረ፤ እንዲህ ያለው ሁናቴ እንዳይደገም ለተናጋሪው ምክርዎን ያካፍሉ። ይህ የጠላት ሥራ ነው። በወገኖች ላይ ጉዳት የሚያስከትል መልእክት የእግዚአብሔር ቃል እንደሚከለክል በትህትና ለተናጋሪው ያስታውቁ።"– Ellen G. White, Ye Shall Receive Power, p. 76.

## የመወያያ ጥያቄዎች

- በሐሙስ ትምህርት ራስን ስለ መግዛት አስፈላጊነት በቀረበው የመጨረሻ ጥያቄ ላይ ተወያዩ። በጸጋ የዳንን ሆነን ሳለ በኃጢአት ላይ አሸናፊ መሆናችን ያስፈለገው ለምንድን ነው? ደግሞስ ወንጌል የሚናገረው ስለ ኃጢአት ይቅርታ አይደል? ከዚህ ሃሳብ ጋር በተያያዘ ስለ ይሁዳ ጸባይና የአጉል ምኞት ኃጢአት ስላደረሰበት ነገር ያስቡ። በኃጢአት ላይ ባለ ድል ልንሆን እንደሚገባ ከላይ ለተነሳው ጥያቄ ከእርሱ ምሳሌ ምን መማር እንችላለን? "አንዲት ፈር የለቀቀች ጸባይ ወይም በልብ ያደረ አጉል ምኞት በስተመጨረሻ መላውን የወንጌል ኃይል ከንቱ ሊያስቀረው ይችላል።"– Testimonies for the Church, vol. 5, p. 53. በኃጢአት ላይ ባለ ድል ልንሆን እንደሚገባ አስመልክቶ መልእክቱ በቀረበው ሃሳብ ላይ ብርሃን መፈንጠቅ የሚችለው እንዴት ነው?
- የመንፈስ ፍሬ ከማንኛውም የመንፈስ ስጦታ ይልቅ በእጅጉ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?
- 1ቆሮ. ምዕ. 13 ያንብቡና በሃሳቡ ላይ ተወያዩ። ጳውሎስ ከሁሉ በላቀ